# መለስ የሚመኘው

አገሬ ከስዊድን
ነሀሴ 2012

ሰሞኑን ″ኑዛዜ አቀርባለሁ″ በሚል ርዕስ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ለ21 አመት በግፍና በጭቆና እንደፈለገው ረግጦ እያስጨነቀ ሲገዛና አገሪቱን ሲቦረቡር የኖረውን የመለስን ሀውልት ለትውስታ እንዲቆም የሚያሳስብ የሚመስል ግጥም ″ከተስፋሁን ሞላ″ ተፅፎ ለንባብ በቅቷል። እኔ ግጥሙን ደጋግሜ አንብቤው ለመረዳት ብሞክርም በጣም የተሸፋፈነ ስለመሰለኝ የድርሻየን ልወጣ በሚመስል ″መለስ የሚመኘው″ በሚል ርዕስ የመልስ ግጥም ለማዘጋጀት ተገደድኩ ። ለዚህም መንደርደሪያ የሆነኝ አቶ መለስ አሁን በህይወት ካለ ሊያስብ የሚችለው ነገር ምን እንደሚሆን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ።

ይድረስ ለገጣሚው ፤ ኑዛዜ ተቀባይ
መለስን አይተነው ፤ በአለም አደባባይ
እንዲያ ሲደነግጥ ፤ ነፍሱ ስትሰቃይ
እንኳንስ በቁሙ ፤ ሀውልቱን ሊያስብ
መታየት አይሻም ፤ በኢትዮጵያ ህዝብ ።
ውነት አይመስለኝም ፤ የኑዛዜው ዜና
እንኳንስ ደንግጦ ፤ ተይዞ በጠና
ውነትን አያውቅም ፤ እያለም በጤና ።

መለስን ለሚያውቀው ፤ ያንን አስመሳይ
አማካሪው ከሆንክ ፤ የሱ ተታላይ
ከሀውልቱ በፊት ፤ ከዓለም ሳይለይ
ጣረሞት ሲይዘው ፤ እጅግ ሲሰቃይ
እስላም ክርስቲያኑ ፤ እያለ መለስ
በፈቀደ ነበር ፤ ለህዝቡ እንዲደርስ
በፀሎት ልብ ሆኖ ፤ እንዲመላለስ ።

የምን ሀውልት ነው? የምንስ ትውስታ?
ባገር ያላገጠ ፤ በጣር ሲንገላታ
የዛሬው ምኞቱ ፤ አልጋ ላይ እያለ
ትንሽ ዕድሜ ነበር ፤ ከእግዜር ከታደለ ።

የተጠየፈው ህዝብ ፤ እጅግ የናቀው
ተመስገን ስላለ ፤ አምላክ ሲቀጣው
ይታየኛል መለስ ፤ ያ ያልጋ ቁራኛ
ቁጭቱ ንዴቱ ፤ ብሎት አላስተኛ
ከህመሙ ጋራ ፤ አዝሎ ቁጭቱን
እድሜውን ሲማፀን ፤ ከምድር ሊያጠፋን ።

መለስ ተረድቶታል ፤ ገና እንደታመመ
በኢትዮጵያ ምድር ፤ ሀውልቱ ከቆመ
አይነጋም ለኢትዮጵያ ፣ ሁሌ እንደጨለመ
ምፅአት እንደሚደርስ ፤ እንደተረገመ ።

ለኔም የሚሰማኝ ፤ ህዝቡም የገባዉ
ባይሆን ቢሳካለት ፤ በለስ ቢቀናው
ምኞቱ መሻቱ ፤ በልቡ ያለው
እንዳልነበር አርጎ ፤ አፈር ማስገጥ ነው።